# Newstart Allowance (የሥራ ፈላጊዎች አበል) እያገኙ በመሥራት ላይ ነዎትን?



We speak your language ☎ 13 1202

*Are you receiving Newstart Allowance and working?* – Amharic

ምን ያህል Newstart Allowance（የሥራ ፈላጊዎች አበል）ሊከፈልዎት እንደሚገባ ለማስላት እንድንችል፣ የእርስዎ ሁኔታ ሲቀየር ማወቅ ይኖርብናል።

የሚከተሉት ያስተውሉ :

- እርስዎ ወይም የትዳር ጓደኛዎ ሥራ ሲጀምሩ ማሳወቅ
- በየሁለት ሳምንት የአበል መጠየቂያ ቅጽ ላይ በየቀኑ ከሥራ የሚያገኙትን የገቢ መጠን፣ ምንም እንኳን ገና ባይከፈልዎትም መሙላት ይገባዎታል
- ምን ያህል ሰዓታት እንደሠሩ ማሳወቅ
- **ጠቅላላ** ገቢዎን ማሳወቅ። ይህ የታክስና ሌሎች ተቀናናሽ ከመቆረጡ በፊት የሚያገኙትን የክፍያ መጠን ማለት ይሆናል።
- የአበል መጠየቂያ ቅጹን በየ 4, 6, 8, 10 ወይም 12 ሳምንታት የሚያስገቡ ከሆነ እና ሌላ ገቢ ከአልዎት፣ ወዲያውኑ በስልክ **13 1202** በመደወል ማሳወቅ
- በሰዓት ምን ያህል ክፍያ እንደሚያገኙ ለቀጣሪ ድርጅትዎ መጠየቅ ይህም የቅጣት ወይም የትርፍ ሰዓት ክፍያ መጠንንና ማንኛውንም አበል ያካተተ ይሆናል
- በየሁለት ሳምንቱ የአበል መጠየቂያ ቅጽ ሲያስገቡ የክፍያ ወረቀትዎንም አብረው ማያያዝ
- እርስዎ ወይም ባለቤትዎ ከአንድ በላይ ቀጣሪ ድርጅት ካላችሁ ከእያንዳንዱ ቀጣሪ ምን ያህል ክፍያ እንደምታገኙ የገቢአችሁን መጠን ማሳወቅ
  – ለማንኛውም የ Centrelink ጽ/ቤት ስለ Casual Income Record（በግዚያዊ ሥራ የሚገኝ የገቢ መዝገብ）መጠየቅ። የሚያገኙትን ገቢ እንዲመዘግቡ ሊረዳዎት ይችላል።
- የአበል መጠየቂያ ቅጽ የሚያስገቡበትና ከአስሪዎ ደምወዝ የሚያገኙበት ቀን አንድ እንዲሆን ከፈለጉ ቀኑን እንድንቀይርልዎት መጠየቅ ይችላሉ።

እርስዎ ወይም ባለቤትዎ የሚያጋጥማችሁን ለውጦች እንደ አስፈላጊነቱ ካልነገራችሁን፣ የሚከተሉት ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ፣

- ክፍያዎ ይቆማል ወይም ይዘገያል፣ **እና/ወይም**
- ከአግባብ በላይ በመከፈል መልሰው እንዲከፍሉት ይደረጋል፣ **እና/ወይም**
- የወሰዱትን እላፊ ክፍያ ለማስመለስ እንደ ሁኔታው እየታየ እዳ የመስብሰቢያ ገንዘብ ክፍያ በተጨማሪ ያስከትላል።

*ሥራ በመሥራት ያለዎትን የተሳትፎ እንቅስቃሴ መመዘኛ* የሚያሟሉ ከሆነ እና በሁለት ሳምንት ውስጥ የሠሩት ከ30 ሰዓታት በታች ከሆነ በቀጥታ Centrelink እንዲያውቅ ማድረግ አለብዎት።

በራስዎ ቋንቋ በይበልጥ ለመረዳት **13 1202*** ን ደውለው ይጠይቁ:: በ ኢንተርኔት ድር፣ **www.centrelink.gov.au** መረጃ ማግኘት ይቻላል::

** በ '13' ለሚጀምሩ ቁጥሮች ከቤትዎ ወይም የህዝብ ቴሌፎን ሲደውሉ ወጪው የአካባቢን ጥሪ ዋጋ ያህል ያስወጣል:: ቢሆንም፡ የጥሪው ሂሳብ እንደ ቴለፎን አገልግሎቱ ድርጅት ዓይነት ሊጨምርም፡ ሊቀንስም ይችላል:: በ '1800' ወደ ሚጀምሩ ቁጥሮች ከቤትዎ ወይም ከህዝብ ቴሌፎን ሲደውሉ የአካባበዎን ጥሪ ዋጋ ያስወጣዎታል:: ከህዝብ ቴለፎንና ሞባይል የተደረገ ጥሪ ይበልጥ ያስወጣል::*

www.centrelink.gov.au

Australian Government

Centrelink giving you options